**ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ትብብር ለፍትኅ**

**Global United Ethiopians Movement for Justice**

# በሞጣ ከተማ የደረሰውን የመስጊዶች መቃጠልና ንብረት መውደም አጥብቀን እናወግዛለን

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያዉያን ትብብር ለፍትሳ በታህሳስ ፲ ቀን በምስራቅ ጎጃም ዞን በምትገኘው በሞጣ ከተማ የሶስት መስጊዶች መቃጠልን የበርካታ የሙስሊም ወገኖች ንግድ ቤቶች ዘረፋና ከፍተኛ ጉዳት መድረስ አጥብቆ ያወግዛል ። ለዚህ አይነት እጅግ አስነዋሪ ወንጀል መፈጸም ምክንያት ሊሆን ይችላል ተብሎ እየተገመተ ያለው በእለቱ መስጊዶች ከመቃጠላቸው ትንሽ ቀደም ብሎ በከተማው ውስጥ በሚገኘው የቅዱስ ጊዮርጊስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ላይ የቃጠሎ አደጋ ደርሶበት ብዙ ጉዳት ከማድረሱ በፊት በህዝብ ርብርብ እሳቱ ከጠፋ በኋላ ከተለያዩ ምንጮች እንደተረዳነዉ ቤተክርስቲያኑ የተቃጠለዉ በሙስሊሞች ነዉ በሚል ቅስቀሳ ተነሳስቶ ወዲያዉኑ በከተማው ውስጥ የነበሩ ፫ መስጊዶች ተቃጥለዋል ብዙ ቁጥር ያላቸው የንግድ ቤቶች ቤቶች ተዘርፈዋል ፣ ጉዳትም ደርሶባቸዋል ። እዚህ ላይ ዋናው ጥያቄ በሌሎች የሐገሪቱ ክፍሎች እንደታዩት ብሄርን ከብሄር ፣ ሃይማኖትን ከሃይማኖት ማጋጨት አላማ አድርገው በተነሱት አጥፊ ኃይሎች በተጠና ሁኔታ የተቀነባበረ ወንጀል ነው ወይንስ በቤተክርስቲያኑ መቃጠል ጋር በተያያዘ አሳሳች ቅስቀሳ ብቻ በግብታዊነት በስሜት በመገፋት የተፈጸመ ወንጀል ? ይህ ጉዳይ በጥብቅ ምርመራ የሚረጋገጥ ይሆናል ። ሆኖም በየትኛውም መልኩ ቢሆን ይህን መሰል አደገኛ ወንጀል በሙስሊም ወገኖቻችን የእምነት ተቋማትና ንብረታቸው ላይ መፈጸሙ እጅግ አሳዝኖናል ፣ አስቆጥቶናልም ።

እዚህ ላይ አንድ በጥብቅ መመርመር ያለበት ጉዳይ ቢኖር ይህ ወንጀል ከመፈጸሙ ከአንድ ወር በፊት የሞጣ ከተማ የሙስሊሙ ማህበረሰብ አስተባባሪ ኮሚቴ ለከተማው አስተዳደር ለዞኑና ለክልሉ አመራሮች ቅድመ ማስጠንቀቂያ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ጥቆማ የሰጠ ሲሆን ነገር ግን በየትኛውም የአመራር እርከን ትኩረት ሳይሰጠው ቀርቷል ። ይህ ለምን ሆነ ? ምርመራው በጊዜው ተካሂዶ ቢሆን ምናልባት ይህንን ወንጀል ከመፈጸሙ በፊት ማምከን ወይንም ጉዳቱን ለመቀነስ በተቻለ ነበር ። ይህ ጉዳይ በጥብቅ መመርመር አለበት ብለን እናምናለን። ተጠያቂ የመንግስት አካላትም ለፍርድ መቅረብ አለባቸዉ። የመስጊዶች ቃጠሎ ከመድረሱ ከአንድ ሳምንት በፊት በሞጣ ከተማ በርከት ያሉ ሚስጥራዊ ስብሰባዎች ተካሂደዋል ፣ የሚሉ ዜናዎች እየወጡ በመሆናቸው ይህ ሁኔታ በወንጀሉ መርማሪዎች ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት መመርመር ይኖርበታል ።


**ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ትብብር ለፍትኅ**

***ሥሙ በግልጽ እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ ውስጥ ፍትህ እንዲሰፍን የሚሰራ ፤ ከዚህ በፊት ዛሬ ወይም ነገ ፍትህ ሲጓደል ለኢትዮጵያ መንግሥትና ህዝብ እንዲሁም ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የማሳየት እና የተጓደለው ፍትኅ አስተማማኝ በሆነ መልኩ እንዲሟላ የሚሰራ አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ነው ።***

POBOX 3005 Tucker GA. 30085

mailto:guethio.4justice@gmail.com

ለመሆኑ የብሄራዊ የሐገር ደህንነት፣ የክልል የሕዝዝብ ደህንነትና የፖሊስ ኃይል እንዲህ አይነትና መሰል ወንጀሎች ከመፈጸማቸው በፊት የማምከን ሃላፊነታቸውን በብቃት የሚወጡት መቼ ነው ? እዚህ ላይ ትኩተር ተሰጥቶ መታየት ያለበት የጊዮርጊስን ቤት ክርስቲያን ቃጠሎው ደርሶበት በሕዝብ ርብርብ ከተገታስ በኋላስ ወዲያው የሃይማኖት ተቋማት ፣ የንግድ አካባቢዎች ለምን በአስቸኳይ በፖሊስ ጥበቃ ስር አልሆኑም ? መልስ የሚሻ ጥያቄ ነው ።

እንደሚታወቀው የጎጃም ሕዝብ ብሎም መላዉ የአማራ ሕዝብ ክርስቲያን ሙስሊም ብሎ ሳይለያይ ደስታውንም ሆነ መከራውን አብሮ እየተካፈለ የኖረ ሕዝብ ነው። ይህ ከሺህ ዘመናት በላይ የቆየ ተከባብሮና

ተባብሮ የመኖር ባህሉ ነው። ነገር ግን ይህንን የመሰለ አስነዋሪ ወንጀል እንዴት እዚያ ሊፈጸም ቻለ ? ጥልቅ ምርምርራ ተካሂዶበት አስቸኳይ መልስ የሚሻ ጥያቄ ነው ። ከሕዝቡ ባህል ውጪ በሆነ መልኩ የተቃጠሉ መስጊዶችን ዙሪያ ከቦ መጨፈር ከየት መጣ ? በእውነት ይህ የሞጣን ነዋሪ ይገልጻል ፡፡ የሆነው ሆኖ የዞኑንና የክልሉ የጸጥታ አካላት በመቀናጀት በወንጀሉ የተጠረጠሩትን እየያዙ መሆኑን ተጎጂው ማሕበረሰብ ፍትሕ እንዲያገኝ ጥረት እያደረጉ መሆኑን ያሳያል። እንደዚሁም የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ (አብን)የአማራ ምሁራን መማክርት ጉባኤ ፣ የአማራ ወጣቶች ማሕበር ፣ ሌሎች ታዋቂ ፖለቲከኞችና ግለሰቦች የተፈጸመውን ወንጀል በአስቸኳይ ማውገዛቸው የሚያበረታታ እርምጃ ነው ። እነዚህ አካላት ከማውገዝ ባሻገር ወንጀሉ በማን እንደተቀነባበረና እንደተፈጸመ ጊዜ ሳይወስድ እንዲታወቅ ለመርዳት ለመርማሪዎች አስፈላጊውን ትብብር ማድረግም ይጠበቅባቸዋል ። የአማራ ክልል ህዝብም በተለያዩ ከተሞች ሰላማዊ ሰልፍ በመዉጣት ማዉገዙ ሊመሰገን ይገባል።

ሌላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ወንጀሉን ከማውገዝም አልፋ ፫ ሊቃነ ጳጳሳት የያዘ ልዑክ ወደ ሞጣ ከተማ በመላክ የተቃጠለውን ቤተክርስቲያን ፣ የተቃጠሉትን መስጊዶች ፣ የወደሙትን የንግድ ቤቶች ከጎበኙ በኋላ ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖቻችንን አግኝተው በማበረታታት ጥያቄያቸውን በመስማት ለጥያቄያቸውም በሚቻለው ሁሉ መልስ ለማግኘት እንደሚጥሩና ሕዝቡ የቆየ አንድነቱን በመጠበቅ ሙስሊም ክርስቲያን ሳይል የኖረበትን አብሮነቱን እንዲያጠናክር መክረው የመስጊዶችንና የወደሙትን የንግድ ቤቶች በአንድነት ሕዝቡ መልሶ እንዲሰራ ጥሪ ማድረጋቸው ከሃይማኖት አባቶች የሚገባውን መፈጸማቸው የሚያስመሰግን ተግባር ነው ።

**ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ትብብር ለፍትኅ**

***ሥሙ በግልጽ እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ ውስጥ ፍትህ እንዲሰፍን የሚሰራ ፤ ከዚህ በፊት ዛሬ ወይም ነገ ፍትህ ሲጓደል ለኢትዮጵያ መንግሥትና ህዝብ እንዲሁም ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የማሳየት እና የተጓደለው ፍትኅ አስተማማኝ በሆነ መልኩ እንዲሟላ የሚሰራ አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ነው ።***

POBOX 3005 Tucker GA. 30085

mailto:guethio.4justice@gmail.com

# ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ትብብር ለፍትኅ

## Global United Ethiopians Movement for Justice

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳይ ጠቅላይ ምክር ቤት የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ለወሰደቸው አቋምና ተግባራዊ እርምጃዎች ምስጋና ማቅረቡ ተገቢና የሚያስመሰግን ተግባር ነው ።

ይህን አስመልክቶ የዓለም አቀፍ ኢትዮጵያውያን ትብብር ለፍትሳ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያቀርባል ።

፩ የተፈጸሙት ወንጀሎች ሁሉ በማን እንደተቀነባበሩና ፣ እንደተፈጸሙ ጥልቅ ምርመራ ተካሂዶበት ወንጀለኞች ሁሉ በአስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርቡ እንጠይቃለን ።

፪ የአማራ ክልላዊ መንግስት ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር ለማዋል ያሳየዉ ጥሩ ጅማሮ እንዳለ ሆኖ ይፋ የሆነ መግለጫ በአስቸኳይ መስጠት ይጠበቅበታል።

፫ የተቃጠሉ መስጊዶችን ፣ የተዘረፉና የተጎዱ ንግድ ቤቶችን መንግሥት እንዲያሰራ እንጠይቃለን ።

፬ ካሳ ለሚገባቸው ካሳ እንዲያገኙ እንጠይቃለን ።

፭ መጠነኛ ቃጠሎ የደረሰበት ቤተክርስቲያንም እንዲጠገን ።

፮ እንደዚሁም በቅርቡ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በርካታ የተቃጠሉ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትና መስጊዶች የፌደራልና ቃጠሎዉ የተፈፀመባቸዉ ክልሎች በመቀናጀት እንዲያሰሩ እንጠይቃለን።

፯ በሞጣ ከተማ በመስጊዶች ላይ የደረሰውን ጥፋት ለማውገዝ ሰልፍ በወጡ አንዳንድ ቦታዎች ተንኳሽና ቀስቃሽ ሃይማኖትን ከሃይማኖት ሕዝብን ከሕዝብ ለከፍተኛ ግጭት የሚያነሳሱ መልዕክቶች ለምሳሌ

መስጊድ ከሚፈርስ ኢትዮጵያ ትፍረስ ፣ አትነሳም ወይ ቁራን ሲቃጠል የአንተ አይደለም ወይ ፣ ቤተክርስቲያኖችን አናቃጥልም ወደ መስጊድነት እንቀይራቸዋለን ወዘተ የሚሉት ወደ ከፋ መተላለቅ የሚወስድ ስለሆነ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራበት በአጽንዖት እንጠይቃለን ።

፰ ከሞጣ ከተማ ዉጭ የምትኖሩ ሙስሊምም ሆነ ክርስቲያን ወገኖች ለደረሰዉ ችግር መፍትሄ የሚያመጣ የማስታረቅና የመርዳት ስራ እንጂ ፀብ ከሚያጭር አብሮነትን ከሚያናጋ ድርጊት እንድትቆጠቡ ከአክብሮት ጋር ወገናዊ ጥሪ እናቀርባለን።

**ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያውያን ትብብር ለፍትኅ**

***ሥሙ በግልጽ እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ ውስጥ ፍትህ እንዲሰፍን የሚሰራ ፤ ከዚህ በፊት ዛሬ ወይም ነገ ፍትህ ሲጓደል ለኢትዮጵያ መንግሥትና ህዝብ እንዲሁም ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የማሳየት እና የተጓደለው ፍትኅ አስተማማኝ በሆነ መልኩ እንዲሟላ የሚሰራ አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ነው ።***

POBOX 3005 Tucker GA. 30085

mailto:guethio.4justice@gmail.com

፱ የሱማሊያ ክልል መንግሥት የውግዘት መልዕክት ለማስተላለፍ በጅጅጋ ከተማ የወጣውን ሰላማዊ ሰልፍ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ ለመውሰድ የፈለጉ ኃይሎች ዓላማ እንዳይሳካ የወሰደው የጥንቃቄ እርምጃና ቁርጠኛ የሆነ የሕግ ማስከበር እርምጃ ሌሎች የክልል መንግሥታትና የጸጥታ አካላት ትምህርት እንዲወስዱ እናሳስባለን ።

፲ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ፣ ካህናት ፣ መምሕራንና ሊቃውንት እንዲሁም በኢትዮጵያ እስልምና ሃይማኖት መሪዎች መምሕራንና ሊቃውንት መካከል ጥልቅ ውይይት በማካሄድ ሕዝቡ ዕምነቱን እንደያዘ ተባብሮና ተከባብሮ እንዲኖር ሐገሩንም እንዲገነባ እንዲያሳስቡት በተለይም ወጣቱን ትውልድ ስለመቻቻል እንዲያስተምሩት ጥሪ እናቀርባለን ።

ለሞጣ ከተማና አጎራባች ቀበሌ ነዋሪዎች ያለን መልዕክት ማንም ሳይነግራችሁ ለዘመናት ደስታችሁንም ፣ ችግራችሁንም እየተጋራችሁ እንደኖራችሁ ማሕበረሰብ ክርስቲያን ሙስሊም ሳትባባሉ ይህን አስቸጋሪና ፈታኝ ጊዜ በትዕግስት በመከባበርና በመተባበር መሻገር ግድ ይላችኋል ።

የተቃጠለውን ሁሉ አብራችሁ በመገንባት ጠላት የደገሰላችሁን የመከፋፈልና የመጠፋፋት ሴራ በማክሸፍ ልታሳፍሩት ይገባል ። ሌላ አማራጭም የላችሁም ። አባቶቻችሁ ከዚያም የቆዩት ያወረሷችሁ አብሮነትንና አንድነትን ነውና ተባብራችሁ መስጊዱንም ቤተ ክርስቲያኑንም እንደምትሰሩት የወደመውን ንብረትም እንደምትተኩት ቅንጣት ያክል ጥርጥር የለንም ።ጅምራችሁም ተስፋ ሰጪ ነዉ።አንድ የሞጣ ተወላጅ የሆኑ ባለሀብት ቤተክርስታያኑንና መስጊዶቹን ለማሰራት የለገሱት ገንዘብ በመልካም አርያነቱ የሚጠቀስ ነዉ።

እዚህ ላይ ሳንጠቅስ የማናልፈው ጉዳይ ቢኖር በቅርቡ በአቶ ጃዋር መሐመድ አነሳሽነት እራሱን ቄሮ ብሎ የሚጠራው ጽንፈኛ የሽብር ቡድን በኦሮሚያ ክልል በፈጸመው ሽብር ፹፮ አብዛኛው ክርስቲያንና ሙስሊም ወገኖቻችን ዘግናኝ ጭፍጨፋ ሲፈጸም ሺዎች ሲፈናቀሉ ይህንን አሰቃቂ ወንጀል የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥትም ሆነ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ፣ አባ ገዳዎች ወይንም ሌላ አደረጃጀቶች ምንም አይነት ውግዘት ሳያደርሱ መቅረታቸው በንጽጽር ሲታይ አግራሞትን ከመፍጠር አልፎ ድርጊቱን ደግፈውታል ወይንስ ተባባሪዎች ነበሩን የሚሉ ጥያቄዎችን ያጭራል ።

ሌላውም ለፍትሕ እታገላለሁ የሚል ስብስብም ሆነ ግለሰቦች በማንኛውም ዜጋ የማሕበረሰብ የእምነት ተከታይ ወይንም ተቋማት ላይ ወንጀል ሲፈጸም ያለምንም አድሎዓዊነት ወንጀሉን



POBOX 3005 Tucker GA. 30085

mailto:guethio.4justice@gmail.com

ማውገዝ የውዴታ ግዴታ መሆኑን ልናስገነዝብ እንወዳለን ። እንዲያውም አንድ የፍትሕ ታጋይ ለዜጋው ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጆች ሁሉ መብት መከበር ዘብ መቆም ዋናው ተግባሩ ነውና ።

የኢትዮጵያ መንግሥትም ይህን መሰል ለሐገራችን ሕዝብ ባዕድ የሆነ የእምነት ቦታዎችን ማቃጠል ፣ የሃይማኖት አባቶችንና ምዕመናንን መግደል የመሳሰሉ ዘግናኝ ወንጀሎችን ከምንጫቸው ለማድረቅ የወንጀሎችን ጠንሳሽና አቀነባባሪ ኃይሎችን በጥብቅ መርምሮ በቁጥጥር ስር አውሎ ለፍርድ እስካላቀረበ ድረስ በባሰ ሁኔታ የሚቀጥል መሆኑን ተገንዝቦ አስቸኳይና የተጠና እርምጃ እንዲወስድ በአጽንዖት እንጠይቃለን ።

ለዓለም ሕዝብ አይነተኛ ምሳሌ ሆኖ የሚጠቀሰው የኢትዮጵያ ክርስቲያኖቸና ሙስሊሞቸ የጠበቀ ሕብረት መከባበርና አንድነት ለዘላለም ይኑር ።



POBOX 3005 Tucker GA. 30085

mailto:guethio.4justice@gmail.com